# ታሪክ ተደገመ

የትግሬው ወያኔ ፣ እስከ ጥግ ገፍቶን
አመፁ ጠንክሮ ፣ በግፈኞች ከፍቶን
የትግላችን ፍሬ ፣ ላኩሪ ድል አብቅቶን
ጥሩ ምላስ ያለው ፣ ትረካው አስቶን
ተምኔታዊ ዓለም ውስጥ ፣ ሰመመን ውስጥ ከቶን
ባራቱም ማዕዘን ፣ እሳት ሲነድ እቶን
ቆም ብሎ ማሰብ ፣ መጠየቅ አቅቶን
ምላሱን አምነነው ፣ ልቡ መቼ ታይቶን
አቢቹ ይፈተሽ ፣ ብንልስ ማን ሰምቶን ።

ከአሩሲ ባሌ ፣ ከጅማ ወለጋ
የዘር ሰንሰለቱ ፣ እየተዘረጋ
በመደመር ስሌት ፣ ህዝብ እያዘናጋ
ኢትዮጵያን ማወደስ ፣ ደጋፊ ፍለጋ
ዲስኩር ስለአንድነት ፣ ሰው እንዲረጋጋ
ከአሜሪካ አውሮፓ ፣ ተሰፈኛ ቢንጋጋ
ሃጎስን ሲተካው ፣ የአቢቹ መንጋ
ለጠባቦች ዛሬም ፣ በሩ መች ተዘጋ
ዛሬም እንዳለ ነው ፣ የትላንቱ አደጋ
ሥጋን ማን ይቀማል ፣ ካራዊት መንጋጋ
በእንጭጭ ካልተቀጨ ፣ ያስከፍላል ዋጋ ።

የበግ ለምድ ለብሶ ፣ የዘውጌ ደላላ
ቂቤ እየጠበሰ ፣ ባፉ ጤፍ ሲቆላ
የምኞት እንጀራ ፣ ጠፍጥፎ እያበላ
በምድር ላይ ያለው ፣ እውነታው ግን ሌላ
የመደመር ነገር ፣ እንዲህ ነው ሲሰላ
አትቆረጠምም ፣ አድራ እቺ ባቄላ
አመልና ጭራ ፣ ሊታይ ወደኋላ
ማጨብጨብ አቁመን ፣ እንጓዝ በመላ ።

የንጉሱ ስርአት ፣ ሲወገድ በደርጉ
ሲጨበጨብ ነበር ፣ ብለን ደግ አረጉ
ደርግ ተወግዶ ፣ ወያኔም ሲገባ
እንደለመደብን ፣ ድጋሚ ጭብጨባ
አሁንም ጉልቻ ፣ ስለተቀየረ
እኛ የምንወደውን ፣ ስለተናገረ
ጭብጨባው ይቀልጣል ፣ ድስቱ እያረረ
ካለፈው ታሪኩ ፣ የለም የተማረ ።

ከእሳት ወደረመጥ ፣ እንደተረገመ
ወርቅነህ አርከበን ፣ አዝሎ የተሸከመ
በአዲስ አበቤው ላይ ፣ ጎጠኛን የሾመ
ነባር አፈናቅሎ ፣ መጤን ያስከተመ
ዛሬም በነ አቢቹ ፣ ታሪክ ተደገመ
ከዝንብ ማር የለም ፣ አለቀ አከተመ ።

ታዛቢው

February 7, 2019